# “ጅብ በማይታወቅበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል።”

## የአባ ማትያስ የግብፅ ጉብኝት፡- የፖለቲካ ተልእኮ

# ክፍል አንድ


ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ

nigatuasteraye@gmail.com


የካቲት 2 ቀን 2 ሺ ፯ ዓ.ም.

“ጅብ በማይታወቅበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ ይላል” የሚለው ጥሬ ንባብ፤ ስለ ጅብና ስለ ቁርበት መልእክት ለማስተላለፍ አይደለም። ጅቡ የሚወክለው አካል አለ። ቁርበቱ የሚወክለው ነገር አለ። በቁርበቱና በጅቡ መካከል ያለውን ግንኙነት ሳያውቁ ቁርበቱን ለጅቡ ያነጠፉለትም የሚወክሉት አለ። ይህ አገላለጽ በኢትዮጵያዊው ቅኔ ትምህርት፣ ቀመር፣ ስልት ሲመዘን፤ ጅቡ ሰም ነው። ቆርበቱም ሰም ነው። ሁሉም ሰም ነው። ወርቁ ከሰሙ ጋራ ጎን ለጎን ባለመቀመጡ፤ ወርቅ የጎደለው ‘ሰማ-ሰም’ ይባላል።

ወደ ጠቅላላ ይዘቱ ስንገባ፤ በጅብና በቁርበት መካከል ያለው ግንኙነት፤ በተበይና በበይ መካከል ባለው ግንኙነት ብቻ ሳይወሰን፤ የተደራረበ ሰይጣናዊ የአጠቃቀምን ዘዴ ይጠቁማል። ጅብ ቁርበቷን እንደሚበላት በማይታወቅበት አገር ሄዶ ቁርበቷን *‘አንጥፉልኝ’* እንደሚል፤ አንዳንድ ሰዎችም በሚታወቁበት አገር ቢያደርጉትና ቢሰሩት ተቀባይነት የማያገኙበትን፤ ይልቁንም የሚዋረዱበትን ነገር፤ በማይታወቁበት አገር ሄደው እንዲደረግላቸው የሚፈልጉትን ለማስደረግ የሚጠቀሙበትን ዘዴ ይገልጻል።

ማታለልን ለመንቀፍና የመታለልንና የማታልያንንም ዘዴ ለመግለጽ “ጅብ በማይታወቅበት አገር ሄዶ ቆርበት አንጥፉልኝ ይላል” የሚለውን ሰማ-ሰም ምሳሌያዊ ከእኛ በፊት የነበሩ ኢትዮጵያውያን መጠቀማቸው የጅቡ ባህርይ የሚታይበት ሰው መንቀፍ ተገቢ መሆኑን ለማሳየት ነው። የጅቡን የማታለል ባህርይ ሳያውቁ ቆዳዋን ባነጠፉ ሰዎች ምሳሌነት የሚቀርቡትም፤ አታላይ ሰው ባገሩ ውስጥ የማያገኘውን፤ ይልቁንም የሚነቀፍበትንና የማይመጥነውን ክብር ሳያውቁ በማቅረባቸው ባይነቀፉም፤ መታለላቸውን እንዲያውቁ ሊገለጽላቸው እንደሚገባ ለማስተማርም ነው።

የፊደላችን፤ የስነ ጽሑፋችንና የበጎ ባህላችን ምንጭ የሆነችው ቤተ ክርስቲያናችን በሰጠችን መነጸር ይህን አባባል ስንመለከተው፤ የማታለል ባህርይ መነቀፍ እንዳለበት፤ የሚታለሉ ሰዎችም እንደተታለሉና ዳግም እንዳይታለሉ መነገራቸው አገባብነት እንዳለው እንረዳለን።

ነቀፌታ ተገቢ ባይሆን ኖሮ፤ መገኘት በማይገባው ቦታ አስመስሎ በመግባት ሲያታልል የተገኘውን ሰው፤ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፤ እጅ እግሩን አስራችሁ አውጡት “ (ማቴ 22፡11-13) ባላለ ነበር። ቅዱስ ጳውሎስም “በውጭ ባሉ ሰዎች መፍረድ ምን አግዶኝ። በውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ አትፈርዱምን? በውጭ ባሉት እግዚአብሔር ይፈርድባቸዋል። ክፉውን ከመካከላችሁ አውጡ ” (1ኛ ቆሮ 5፡12 ) ባላለም ነበር። ከቤተ ክርስቲያን ውጭ በሆነ ቡድን ወደ መንፈሳዊ አመራር የሚመጣውንም መንቀፍ ክልክል ቢሆን ኖሮ፤ የቀኖና መጽሐፋችን በምድራዊ ኃይልና ድጋፍ የሰየመውንና የተሰየመውን ምቱራን ( ህይወት አልባ ሆነው የተወለዱ ናቸው) ባላላቸውም ነበር (ፍ.ነ. ፻፸፭) ።

በተሳሳቱ መንገዶች ወደ መንፈሳዊ አመራር ሰርገው በገቡ ሰዎች ላይ የሚሰነዘረውን ነቀፌታ ለመቃወም የሚሞክሩ ብዙ ናቸው። በጅብ ባህርይ ጭልጥ ብለው ከተወሰዱት ሰዎች ይልቅ ያዙን ልቀቁን የሚሉትም የጅቡ ባህርይ መነቀፍ የለበትም የሚሉት ናቸው። እነዚህ ሰዎች በቅዱሳት መጻህፍት የተረጋገጠውን ነቀፌታ መቀበል አይፈልጉም። ይልቁንም መነቀፍ የሚገባውን የጅቡን ባህርይ እየጋረዱ፤ የጅቡን ባህርይ ለሚነቅፈው ሰው፤ የማይስማማውን ቅጽል ይሰጡታል። አንድ ጊዜ “ዘረኛ ነው” ሌላ ጊዜ ከእምነት

ጋራ እያገናኙ ከየዋሁ ህዝብ ጋራ ለማጋጨትም “የማርያም ጠላት ነው” በሌላ ጊዜ ደግሞ “ፖለቲከኛ ነው” ብለው ያስወሩበታል። ይህን በማድረጋቸው ከቅዱሳት መጻሕፍት ጋራ መጋጨታቸውን አይረዱም።

በተሳሳቱ ሰዎች የሚፈጸመውን አስነዋሪ ነገር መንቀፍና አድራጊውን መገሰጽ፤ ቤተ ክርስቲያንን ከፍ የሚያደርጋትና የሚቀድሳት መሆኑ ለመገንዘብ ካቅማቸው በላይ ይሆንባቸዋል። ገነት ውስጥ አዳም ሄዋንና እባብ ተሳሳቱ። የተሳሳቱት አዳም፤ ሄዋን እና እባብ እንደየ ስራቸው ተነቀፉ፤ ከገነትም ወጡ። ገነት ተዘጋችባቸው። ይህም የሚያስተምረው በቤተ ክርስቲያን ተሰውረው አስነቃፊ ነገር የሚሰሩትን ከቤተ ክርስቲያን ለይቶ ለማሳየት የሚደረገው ነቀፋ፤ ተገቢ መሆኑን የሚያሳይ እንደሆነ ለመገንዘብ አቅም ያጥራቸዋል። በዘመናችን በቤተ ክርስቲያን አካባቢ የተከሰቱትን ተነቃፊ ነገሮች ስንነቅፍ፤ ከዘመናችን በፊት የነበረችውን፤ ከዘመናችን በኋላ የምትኖረውን ቤተ ክርስቲያንን መንቀፍ እንደሆነ አድርገው የሚናገሩትን ፤ ባልገባቸው ነገር የሚዳክሩ፤ ለሆዳቸው ያደሩ ተነቃፊዎች ናቸውና ልንሰማቸው አይገባንም።

እንደነዚህ ያሉት ሰዎች “ያላዋቂ ሳሚ ንፍጥ ይለቀልቃል” እንዲል፤ ስለ ባህላችንና እምነታችን ምንም ግንዛቤ የሌላቸው ቤተ ክርስቲያንን ያፈቀሩ የወደዱ በሚመስለው አሳሳች አነጋገራቸው፤ ከተሳሳቱትና ከስህተታቸው ጋራ ቅድስት ቤተ ክርስቲያንን በመደመር ቅድስናዋን የሚያረክሱ ናቸው።

ሊቃውንት አበው እንደሚሉት፦ በምቀኝነት፤ በግል ጥላቻ፤ በጎሳና በተጣመመ ፖለቲካ ካልተበከለ ህሊና የሚመነጭ ነቀፌታ፤ ቢያንስ ለሶስት ነገሮች የሚረዳ መሆኑን ሊማሩ ይገባቸዋል።

- 1ኛ፦ ከእኛ በፊት የነበረችውንና ከእኛም በኋላ የምትኖረውን የቅድስት ቤተ ክርስቲያንን ሰማያዊ ተልእኮ፤ ለምድራዊ ተልእኮ ማስፈጸሚያ በማድረግ ላይ ካሉት ሰዎች ለይቶ ለማሳየት ይረዳል።
- 2ኛ፦ በመሳሪያነት ለምድራዊ ተልእኮ መስሎ የገባውን ሰው ቢቻል መሳሳቱን ተገንዝቦ እንዲመለስ፤ ባይቻል ግን ቦታው አለመሆኑን ተገንዝቦ ቤተ ክርስቲያንን ለቆ እንዲሄድ ለማሳሰብ ይረዳል።
- 3ኛ፦ ስለ ቤተ ክርስቲያናችን ጥልቅ ግንዛቤ የሌላቸው ሰዎች፤ በስህተት የገቡ ሰዎች የሚፈጽሙትን አስነዋሪ ተግባራቸውን እንደምሳሌ በመውሰድ የኑሯቸው ዘይቤ እንዳያደርጉት ይረዳል።

በቅድስት ኦርቶዶክሳዊት ቤተ ክርስቲያናችን መስፈርት ተፈትነው የሚሰየሙ ካህናት፤ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ለምታስተምረው ለእምነት፤ ለስነ ምግባር፤ ለስነልቡና እና ለህዝብ ደህንነት ተላልፎ ለመሞት መለኪያነት የሚጠቀሱ ምሳሌዎችና አብነቶች ለመሆን ነው።

አብነት (አባትነት) የጎደላቸውን ሰብሮ ገብ ካህናትን ከመንቀፍና ከመተቸት ይልቅ፤ ምንም እንዳልጎደላቸው ሸፋፍኖ አለባብሶና አስመስሎ መቀበል፤ የቤተ ክርስቲያንን ገጽ መበከል፤ ክርስቶሳዊ አቋሟንም ማቃወስና ማዋረድ ነውና፤ ካህናት በጠቅላላ ህዝበ ክርስቲያን ላይ ከሚደርሰው ነቀፌታ ይልቅ ለበለጠ ነቀፌታ መጋለጣቸውን አውቀውና ተረድተው የተሰለፉ መሆን አለባቸው “የኦርቶዶክስን ቤተ ክርስቲያን ሰበርናት” እያሉ የፈከሩባትን ሰዎችና በነሱ እየተገፉ የተሰገሰጉትን ሰዎች አለመንቀፍ ፤ በክርስትና ትምህትና በባህላችን ተቀባይነት የሌለው ነውር ነው።

ቄስ፣ መነኩሴ፣ ሰባኪ፣ ፓትርያርክ፣ ብጹዕ፣ ቅዱስ፣ ሊቀ ጳጳስ፣ እጨጌ፣ የመሳሰሉትን የተደራረበ የክብር ስም የተሸከምን ሰዎች፤ ሕብረተ ሰቡ ለእምነቱ ለስነ ባህርዩና ስነ ምግባሩ መለኪያነት አንጋጦ ይመለከተናል። የምንናገረው የምንሰራው ከቅስናችን መስመር አፈንግጦ ከታየብን፤ ሁለት ሰዎች ሆነን ራሳችንን ከራሳችን ጋራ በማጋጨት ላይ ነን ማለት ነው። ፈጦ በመታየት ላይ ያለውን ስህተት መቀበልና አለማውገዝ የፖለቲካ ተልእኮ ሲሆን፤ ይህን መሳይ ባህርይ መንቀፍ፤ አለመቀበልና ማውገዝ ክርስቶሳዊ ተግባር ነው።

ስህተትን መንቀፍ፤ ክርስቶሳዊ ተግባር መሆኑን የተረዱ ሰዎች፤ የክርስቶስ ጸጋ የመንፈስቅዱስ ረድኤት ከውድቀት እንደሚጠብቃቸውና የበለጠ እንዲጠነከሩ እንደሚያደርጋቸው ይታመናሉ። ሰሎሞን “ልቡ ለጻድቅ ውኩል ከመ አንበሳ”(ተግሳጽ 4፥1) እንዳለው፤ መነቀፍን በመፍራት መንቀፍን አይፈሩም። የሚነቀፉበት ስህተት ሲታይባቸው ቢነቀፉ ይማሩበታል፤ ይቅርታ ይጠይቁበታል፤ ንስሀ በመግባት ይጠቀሙበታል። ስማቸውን ደብቀው፤ ጨለማ ለብሰው በሰው ላይ የሀሰት ስም አይለጥፉም። እነሱን በማይገልጣቸው መንገድ አስመሳዮች፤ ሸፍጠኞች፤ አድር ባዮች በግል ጥላቻ ቢነቅፏቸው ደስ ይላቸዋል። በነሱ ከመከበር ይልቅ፤ መነቀፍን ይመርጣሉ።

በቤተ ክርስቲያን ያደጉ ሰዎች ይቅሩና፤ በኢትዮጵያዊው ባህል በተቃኘ ቤተ ሰብ ያደገ ሰው ማንንም ሰው ባልሰራውና በማይመለከተው መንቀፍ፤ በአርያው የፈጠረውን አምላክ ማሳዘን እንደሆነ አይዘነጋም። ለማስረጃነት ከሚጠቀሱት መጻሕፍት፤ ለምሳሌነት ስማቸው ከሚጠራላቸው ንጽህናቸውን ጠብቀው ተልእኳቸውን ፈጽመው ካለፉት አባቶችና እናቶች ጋራም መጋጨት እንደሆነ ያውቃል። ሌላው ቀርቶ የተነቃፊው ሕሊና የማይቀበለውን ነቀፌታ መናገር፤ በሚነቀፉት ሰው ትዝብት መነቀፍም ተገቢ አለመሆኑን ይቀበላል።

ተገቢ ነቀፌታን የሚቃወሙ ሰዎች፤ መታረም፣ መዘለፍና መገሰጽ ለሚገባው ሰው ሽፋን ሲሰጡ፤ ወዳጆቻቸው የሚነቀፉባቸው ትንሽ ስህተት ሲፈጽሙ፤ ፊት ለፊት ከመውቀስና ከመምከር ይልቅ፤ በሌሉበት ስማቸውን እያነሱ ይከሳሉ። "ዘየሀሚ ቢጾ በጽሚት ኪያሁ ሰደድኩ" (መዝሙር 100፡ 9) የሚለውን የእግዚአብሔርን ቃል የማያስተውሉ፤ የልባዊ ወንድምነት ስሜት ያልተቀረጸባቸው፤ ቢጤዎቻቸውን የሚውጡ የእባብ ባህርይ የተጠናወታቸው ናቸው። [*ይህን አስመልክቶ የተጻፈውን ጦማር ሙሉ ሀሳብ ለማንበብ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* የዘንዶ ሱባኤ]

ቀጥ ያለ አቋም የሌላቸው ተሙለጭላጭ ሰዎች "መነቀል ያለበት የተነቃነቀ ጥርስ ናቸው" ከጥንታውያን ሊቃውንት ከእነ ኤልፋዝ፤ በዘመናችን ካሉት Bertrand Russel ከመሳሰሉት መካሪዎችም ጋራ የተጋጩ ከህዝቡና ከእምነቱ ጋራ የተሳሰሩበት ሞራላዊ እትብታቸው የተበጠሰባቸው ናቸው ። ከጥንታውያን ፈላስፎች ኤልፋዝን፤ ከዘመናውያን ደግሞ Russel ን መጥቀሴ፤ ከክርስቶስ ቀጥየ ከጠቀስኳቸው ከክርስቲያኖች ሊቃውንት አብልጫቸው ሳይሆን፤ በተለያየ ግንዛቤ ለሚያነቡ አንባብያን፤ አማራጭ ለማስፋት ብየ ነው።

በኢዮብ ዘመን የነበረ ኤልፋዝ የተባለው ሰው "ቀዳሚሁ ለጥቢብ ያወስእ ዘይሄሊ መንፈሰ። መጠንከ እምቃለ አፉከ። ወኢፈለጥከ ነገረ ዓበይት። ወይዘልፊከ ቃለ አፉከ ወአኮ አነ። ወከናፍሪከ ማኅተትከ። ወምንተ ተአምር ዘኢነአምር ንሕነ ወምንተ ትሌቡ ዘኢንሌቡ ንህነ" (እዮብ 15፡9)። ብሎ እንደተናገረው፤ የተሳሳተ ሰው በሰራውና በተናገረው ብቻ የሚነቀፍበት ምክንያት፤ ከታሪክ፤ ከባህላና ካካባቢው ህዝብ ጋራ መጋጨቱን ለማሳየት ነው።

ኤልፋዝ እንዳለው፤ "ሰው ለሚናገረው ሁሉ ሚዛን ሊኖረው ይገባል። ንግግሩን ከሱ በፊትና ባካባቢው ባሉት አዋቂዎች ለክቶ መናገርን ማወቅ አለበት። ከዚህ ባፈነገጠ ጠባይ በሚናገረውና በሚሰራው ስህተት የታዘበው ሰው ቢዘልፈው፤ ሀላፊነቱ የዘላፊው ሳይሆን፤ የራሱ የተዘላፊው ሰው ነው" ብሎ በተናገረው ላይ አባቶች የሰጡትን ትንታኔ ሳሰላስል ፤ የዘመናችን መካሪ አስተማሪ Bertrand Russel የተባሉት ሰው "on God and Religion" በሚል ርእስ የተናገሩትን አስታወሰኝ።

Russel ክርስቲያን መስለው ስለሚያታልሉ ሰዎች ሲናገሩ፤ "ክርስቲያን ነን የሚሉ ሰወች በፈጣሪ ህልውና እና ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለ ማመናቸው ብቻ በቂ አይደለም። በፈጣሪ ህልውና እና ከሞት በኋላ ህይወት እንዳለማ ከክርስትና እምነት ውጭ ያሉ ሰዎችም ያምናሉ። ክርስቲያኖች በንግግርም በተግባርም ክርስቶስን ለመምሰል ረቀቅ! መጠቅ! በማለት በክርስትና እርከን ላይ መድረስ አለባቸው። በክርስትና እርከን ላይ ካልደረሱ ክርስቲያን ነን በማለት ብቻ በክርስትና ሚዛን ውስጥ መግባት አይገባቸው" (58) አሉ። የ ኤልፋዝም ሆነ የ Russel ምክር፤ ያልሆነውን ሆነን፤ ያልበቃነውን በቅተን፤ ያላመነውን ያመን መስለን መናገር፤ <u>በመመጻደቅ ሰውን ማሳሳት ስለሆነ፤ መወገዝ መገሰጽና መነቀፍ እንጅ መከበርና ተቀባይነት ማግኘት ተገቢ አመሆኑን ያሳያሉ</u>።

'ቡሩክ' ብለን የምንቀበለው ያለ አንዳች ነቀፌታ በእግዚአብሔር ስም የሚመጣውን ብቻ እንጅ፤ ቤተ ክርስቲያንን ሰበርኳት እያለ በሚናገር አቶ ስብሀት ነጋን በመሰሉ ሰዎች ግፊት በቅድስት ቤተ ክርስቲያን ላይ የሚጫነውን ሁሉ፤ የሞራል መለኪያ እንደሌለው ማኒ እየተቀበሉ ማስተናገድ ክርስትና አይቀበለውም።

ማኒ የተባለ ሰው "ቡድህ ለህንድ፤ ዞሮስተር ለፔርሺያ፤ ኢየሱስ ለእስራኤል፤ ራሱ (ማኒ) ደግሞ ለባቢሎን የተላኩ ነኝ ብሎ የሰበከ ሰው ነው። ማኒ 'Our present world is formed by heavenly powers from the chaos of intermingled light and darkness resulting from this struggle' ይህች የምንኖርባት ዓለም ከብርሃንና ከጨለማ ቅልቅልና ድብልቅልቅ በሰማያዊ ኃይል የተሰራች ናት" ይላል። ይህን ትምህርትና እምነት የሚቀበሉ ሰዎች "ሞራለ ቢስነትንና ሞራላዊነትን እያዋሀዱ ማስተናገድ ነው" ብለው ይደመድማሉ።

የማኒን መርሆ የሚከተሉትን ሰዎች፤ መጽሐፋችን <u>'ሠራዊተ መስቴማ'</u> (የሰይጣን ሰራዊቶች) ይላቸዋል። እንደ ማኒ ደቀ መዛብርት ሞራለ ቢስነትንና ሞራላዊነትን እያዳቀሉ ተመልካቾቻቸውን ግራ ያጋባሉ። <u>ራሳቸው የሰሩትም ስህተት እንዳይገለጥባቸው</u>

ጽድቅንና ኃጢአትን አስማምተንና አቻችለን እንኑር እያሉ ይሰብካሉ። በዚህ አይነት ርካሽ ባህርይ የቆሸሹ አስመሳይ ካህናት ለድካማቸው እንደ ማስረጃ የሚጠቅሱት "አንተ ግብዝ አስቀድመህ ባዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታወጣ የወንድምህን ጉድፍ ላውጣ ማለት እንዴት ትችላለህ?" (ማቴ 4:5) ብሎ ክርስቶስ የጠየቀውን ነው። ይህን ጥያቄ መመለስ የምንችለው፡- ከዚህ አረፍተ ነገር ጋራ የተጋጩ የሚመስሉ ራሱ ክርስቶስ የተናገራቸውን ከዚህ በታች የሰፈሩትን ትእዛዞች ስንመለከት ነው።

- 1ኛ፡-"የሰርግ ልብስ ሳትለብስ እንዴት ወደዚህ ገባህ ? እጅ እግሩን አስራችሁ በውጭ ወዳለው ጨለማ አውጡት" (ማቴ 22፡13) ያለውን
- 2ኛ፡- "በመቅደስ የሚሸጡትንና የሚገዙትን ሁሉ ቤቴ የጸሎት ቤት ናት እናንተ ግን የወንበዶችና የሌቦች ዋሻ አደረጋችኋት" (ዮሐ2፡14-16) ብሎ በአታላዮች ላይ ጅራፍ መምዘዙን ስንረዳ ነው።

ታዲያ "አንተ ግብዝ አስቀድመህ ባዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታወጣ የወንድምህን ጉድፍ ላውጣ ማለት እንዴት ትችላለህ": ማለት፡- አንተ የሰራኸው ትልቅ ስህተት እንዳለ ህሊናህ እየመሰከረብህ፤ ትንሽ ስህተት የሰራውን ሰው ለመንቀፍ አትቸኩል ለማለት እንጅ፤ ስህተትን መንቀፍ ትክክል አለመሆኑን የሚያሳይ አይደለም።

በተለይ ካህናት የምንናገረው የምንሰራው ከተሰለፍንበትና ከተሰየምንበት መስመር አፈንግጦ ከታየብንና፤ በተመልካች ዓይን ሁለት ሰዎች ሆነን ራሳችንን ከራሳችን ጋራ እስከማጋጨት ከደረስን፤ አትንቀፉን አትገስጹን ማለት፤ ከክርስትና ትምህርት የራቀ፤ የሰይጣንን ባህርይ የሚያንጸባርቀው የማኚ ተልእኮ ነው።

ህዝቡ መንፈሳዊ ንቃት አግኝቶ፤ ስንሸፍጠው ስናታልለው ደፍሮ እንዳይቋቋመን፤ "እግዚአብሄር የቀባውን አትናገረው" በሚለው ስብከታችን የሚታይብንን ስህተት አፍኑ! ምንም ላለማለት ተጠንቀቁ! እያልን የምንሰብክ ከሆንን እንዴት መንፈሳውያን መሪዎች መሆን እንችላለን? [*ይህን አስመልክቶ የተጻፈውን ጦማር ሙሉ ሀሳብ ለማንበብ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* "እግዚአብሔር የቀባው"]

መጠንቀቅ የሚገባን፤ ራሳችን ከወደቅንበት ስህተት ሳንላቀቅ፤ ከጥጋችን ያለው ወንድማችን በትንሽ ስህተት ወድቆ ስናየው፤ በተጨማሪም በግል ሳንመክረው በሰውም ሳናስመክረው እንፍረድብህ እንዳንል ነው። የሚያስነቅፍ ስራ እየደጋገመ የሚሰራውን መንቀፍ አይደለም። ይህንን አለማድረግማ ! በክርስቶስ ዘንድ ግብነዝነት ነው። የቅስና ዋና ተልእኮ ስህተትን መንቀፍና፤ የተሳሳተውን ሰው ከሚያስነቅፍ ተግባር እያላቀቁ፤ በተግሳጽ መደገፍ ነው።

እነ አቶ ስብሀት ነጋ ወደ ፓትርያርክነቱ እያደንደረደሩ አቡነ ማትያስን ሲወስዱዋቸው፤ አድራጎታችሁ ከመመሪያችን ውጭ ነውና አቁሙ ! መባላቸውን የሚነቅፉ፤ በዚህ አይነት ግፊት ወደ መንበሩ ለመምጣት በፍቅረ ስሜት የሚፈተኑትን ምቱራን ናቸውና አትቀበሏቸው ብላ ቤተ ክርስቲያናችን የምታውጀውንም መመሪያ የሚነቅፉትን፤ ራሳቸሁ ምቱራን ናችሁ እንድንላቸው መመሪያችን ያስገድደናል። ፡፡ [*ይህን አስመልክቶ የተጻፈውን ሙሉን ሀሳብን ለማንበብ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* *"ጭንጋፍ (ምቱር) ፓትርያርክ"* ]

አቡነ ተክለ ሃይማኖትንና አቡነ ማትያስን በቅርብ የሚያውቅ ሰው፤ አቡነ ተክለሃይማኖትን ሲነቅፉ የነበሩትን፤ እጅግ በተጣመመ መንገድ ወደ መንበር ፓትርያርኩ የመጡትን አቡነ ማትያስን አለመንቀፍ፤ የሚያስነቅፍ ትልቅ ስህተት ነው። የአቡነ ማትያስና የአቡነ ተክለሃይማኖት የምንኩስና ሕይወትና ወደ ፓትርያርክነት የመጡበት መንገድ፤ ፈጽሞ የማይገናኝ ሰማይና ምድር መሆኑንም አለመመስከርም በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ተቀባይነት የሌለው ደባ ነው። አቡነ ተክለሃይማኖት ወደ ፓትርያርክነቱ ሲመጡ፤ ፓትርያርክ እንደሚሆኑ ተነግሯቸው፤ ከነ አቦይ ጸሃይ ጋራ እየተወያዩ እንደመጡት እንደ እነ አቡነ ማትያስ በቅድመ ዝግጅት የመጡ አልነበሩም።

የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክነት፤ ሳያውቁት እንደወፍ ተጠምደው የገቡበት ወጥመድ ሲሆን፤ የተሳሳቱት ነገር ቢኖርም ሳያውቁ ያደረጉት ቢሆን እንጅ፤ ህሊናቸው ከተረዳው በኋላ፤ የተሳሳቱ ሰዎች ያጎረሷቸውን ስህተት ውጠው፤ እንደመመሪያ ሊጠቀሙበት ቀርቶ፤ ሳይተፉት ጀንበር አትቀድማቸውም ነበር።

ባንድ ወቅት በጊዜአዊ ተሀድሶ ጉባዔ ዙሪያ የነበሩ ሰዎች፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖትን ባንድ ነገር አሳስተው ለህዝብ እንዲናገሩ ካደረጉ በኋላ፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖትም እንዳሳሳቷቸው ነቅተው በመበሳጨት በተቆጡ ጊዜ፤ ያሳሳቷቸው ሰዎች "ከቅዱስነተዎ

የሚወጣው ውሸት ቢሆንም፤ ህዝቡ ከቅዱስነተዎ ከወጣ ቅዱስ ነው ብሎ ስለሚያምን አይጨነቁበት" እያሉ ውሸቱን ተቀብለው እንዲኖሩ ያደረጉትን ጥረት፤ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ለማክሸፍ ከተቀመጡበት ወንበር ተነስተው ልብሳቸውን አራግፈው ከመኻታ ቤታቸው እንዴት ዘለው እንደገቡ ትዝ ይለኛል። የዛሬው ፓትርያርክ አቡነ ማትያስ አባ ተክለ ማርያም አስራት በሚባለው ስማቸው፤ በአቡነ ቀሲስነት በቦታውና በወቅቱ እዚያው ስለነበሩ፤ አቡነ ተክለሃይማኖት ፓትርያርካዊ ምሳሌነታቸውን የአስነቃፊ ነገር ጠለሸት እንዳይበክልባቸው ምን ያህል ጥንቁቅ እንደነበሩ ያዩትን ባንደበታቸው ባይመሰክሩትም ህሊናቸው የሚክደው አይደለም።

ዶ/ር አረጋዊ በርሄ እንደገለጹት አቡነ ማትያስ የመጡት *"ቤተ ክርስቲያኗ ለረዥም ዘመናት በህዝቡ አዕምሮ ላይ ስትተቀርጸው የኖረችውን ብሄራዊ የኢትዮጵያነትን ስሜት ከትግራይ ህዝብ አዕምሮ ጠራርጎ በጠባቡ ትግሬአዊነት ስሜት በመተካት የቤተ ክርስቲያኒቱን ይዘት እያጠበቡ ቤተ ክርስቲያኒቱን መምታት ነው"* ብለው እነ አቶ መለስ የዘረጉትን የጥፋት መርሆ ተግባራዊ ለማድረግ፤ ከእነ አቶ ስብሀት እና አቦይ ጸሐይ ጋራ ቃል ኪዳን በመግባት ነው።

የዶክተር አረጋዊ ብርሄን መጽሐፍ ያነበቡና "ብጹአን ወኃያላን እለ ትገብሩ ቃሎ። ወእለ ትሰምዑ ቃለ ነገሩ"(መዝሙ 102:40) የሚለውን የዳዊት ቃል የተረዱ "የእግዚአብሄርን ቃል ሰምታችሁ ፈቃዱን የምትፈጽሙ ብጹአን ኃያላን ናችሁ"። የሚለውን መለኮታዊ ተልእኮ ገሸሽ ያደረጉትን፤ ለጸረ ህዝብ ፖለቲካ ሽፋን ለመሆን ተዘጋጅተው ወቅት ሲጠብቁ የነበሩትን አቡነ ማትያስን አለመንቀፍ፤ ህሊናቸው የሚቀበልላቸው አይመስለኝም።

የተዋረዱበት፣ የጎሰቆሉበት፣ የታሰሩበት፣ የተደበደቡበት፣ የተገረፉበት፣ የተሰደዱበት፣ የታፈኑበት፣ የተከፋፈሉበት ይህን የመሰለ የከፋ ዘመን ኢትዮጵያውያንን ገጥሟቸው አያውቅም። አሳዳጁ፣ ገዳዩ፣ አፋኙ፣ ታራሚውና አሸባሪው መንግሥት ለንጹሀን ዜጎች የሚሰጠውን የማፈኛ ስያሜ እየተቀበሉ፤ በህዝቡ ላይ የሚያስተጋቡ እነዚህን የመሰሉ ቀሳውስት ቆሞሳትና ጳጳሳት ከዚህ ቀደም ኢትዮጵያውያንን ገጥሟቸው አያውቅም።

"እግዚአብሔር ሐወጸ እምሰማይ ዲበ ምድር። ከመ ይስማእ ገአሮሙ ለሙቁሀን። ወከመ ያህይዎሙ ለደቂቀ ቅቱላን" (መዝ 101:36) ማለትም፦ "እግዚአብሔር የታሰሩትን ጩኸት ይሰማ ዘንድ የሚገደሉትን ልጆች ይታደግ ዘንድ ቸላ አይልም" የሚለውን የዳዊትን መጽሐፍ መድገም ቀርቶ ሰምተው የማያውቁትን ፤ ገዳማትን ከሚደመስስ፤ ህብረትን ከሚያፈርስ፤ ህዝብን ከሚያፈልስ ቡድን ጋራ የሚተባበሩ መንፈሳውያን መሪዎችን አመጣህብን" ብለው በየገዳማቱ ያሉ አባቶች በመረረ ስሜት የሚያዝኑበት የሚተክዙበትና የሚያለቅሱበት ዘመን ነው። ይህን ክፉ ዘመን አለመግለጽ፤ የዘመኑን ክፋት አለመንቀፍ  እና ፈጻሚዎችን አለመገሰጽ "ከመ ይስማእ ገአሮሙ ለሙቁሀን። ወከመ ያህይዎሙ ለደቂቀ ቅቱላን" የሚለውን የእግዚአብሔርን ርህራሄና ታዳጊነት መካድ ነውና ይህን የማይነቅፍ ኦርቶዶክሳዊ ካህን መነቀፍ ያለበት ሰብሮ ገብ ነው።

ከእምነታችንና ከባህላችን የምንማረው "እኛ በሰላም እየተኛን እየተነሳን ከበላን፣ ከጠጣን፣ ከተመቸን ጊዜያችንን እናሳልፍ" ማለትንና በዘርና በፖለቲካ በግል ጥቅም የማስተዋል ኃይልን ማጨለም ትክክል አለመሆኑን ነው። ነቀፋን ከመረጃ ከእውነት እና ከንጹህ ህሊና በራቀ፤ በግል ጥላቻ ስምን በመሰወር የሰውን ስም በሀሰት የሚያቀርቡትን ወሬ አምኖ መቀበልና ለሌላውም ማስተላለፍ በሰውም በፈጣሪም ይቅርታ የሌለው በደል መሆኑንም ነው። ነቀፋችን ከግል ጥላቻ በመነሳት ብቻ ከሆነ፤ እግዚአብሄር ያለበሰውን ቆዳ መግፈፍ አረመኔነት እንደሆነ ኢትዮጵያውያን ያብነት መምህራን ደጋግመው የሚናገሩት ነው።

በበኩሌ አቡነ ማትያስ የሰሩትንና የሚሰሩትን ስነቅፍ "በነ ፋሌቅ ወጥመድ" ከመግባታቸው በፊት የነበራቸውን የማውቅላቸውን ገርነት የዋህነት ሰውሬ አይደለም። ያም ሆነ ይህ፤ አቡነ ማትያስ "አንተ ግብዝ አስቀድመህ ባዐይንህ ውስጥ ያለውን ግንድ ሳታወጣ የወንድምህን ጉድፍ ላውጣ ማለት እንዴት ትችላለህ?" ብሎ ክርስቶስ የተናገረውን አረፍተ ነገር ቢረዱ ኖሮ፦

- 1ኛ፦ አቡነ ተክለሃይማኖት ያሸከሟቸውን ውግዘት ከራሳቸው ሳያወርዱ
- 2ኛ፦የተሳሳቱትን ነገረ መለኮት ሳያስተካክሉ
- 3ኛ፦ከቤተ ክርስቲያን መመሪያ ውጭ፤ በነ አቶ ስብሀት ወደ መንበር ፓትርያርክ መምጣት ምቁርነት ነውና አትቀበሉት የሚለውንም ጥሰው አይገቡም ነበር።

ይህን ሁሉ ጥሰው ወደ ፓትርያርክነቱ ባይገቡ ኖሮ፤ በውስጥም በውጭም ያለው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚያስተጋባውን ዋይታና ልቅሶ እንዳልሰሙ ሰምተው ባላለፉትም ነበር። እነ አቶ ስብሀት ነጋ በህዝብ ላይ ሚፈጽሙትን ግፍ የሚሸፍኑባቸውን ታራሚና አሸባሪ የመሳሰሉትን ቋንቋዎች ቃለ ቡራኬ እያስመሰሉ በመናገር በህዝቡ ላይ ባልተሳለቁ ነበር።

እውነተኞች ካህናት ቀኖናውን የሚያፈርስ፤ የሰውን ክቡርነት የሚገስስ በዘመናቸው ሲከሰት፤ ግፈኛውን የሚያስገድዱበት ወታደር የሚያስሩበት ወህኒ ባይኖራቸውም፤ አለመንቀፍ አለመውቀስና ከህዝብ ጋራ አለመቆም ከበዳዩ የበለጠ ግፍ መፈጸም መሆኑን ለመረዳት ጊዜ አይወስድባቸውም። "ዘይፈጽም ዕዘኒሁ ከመ ኢይስማእ ነዳያነ፤ ውእቱኒ ይጼውእ ወአልቦ ዘይሰምዖ" (ምሳሌ 21፡13") የተገፉትን ሰዎች ዋይታ ላለመስማት ጆሮውን የሚደፍን፤ እራሱ በመከራ በወደቀበት ጊዜ ሲጮህ ሰሚ አያገኝም "እያሉ የሚያስተምሩበትን ተልእኮ አይክዱም።

ፓትርያርክ ለሀገር አንድነት ለህዝብ ደህንነት ለመሰለፍ ሀላፊነት ቢኖርበትም፤ ኢህዴግ ልማት የሚለውን "የጅብ ፖለቲካ ቁርበት ነጠፋ እንጅ ሰባዊ ፖለቲካ አይደለም" እያሉ በሙያው በቂ እውቀት ያላቸው ኢትዮጵያውያን፤ ላልተቀበሉት ልማት ከመከነፍ ይልቅ፤ "ከሁሉ አስቀድማችሁ የእግዚአብሔርን መንግሥትና ጽድቁን ፈልጉ" ለሚለው ቅድሚያ በመስጠት፤ ራሳቸው የናዱት ነገረ መለኮት፤ የሰረዙት ቀኖና ለሚስተካከልበት ቅድሚያ መስጠት ይገባቸው ነበር። [*ይህን አስመልክቶ የተጻፈውን ሙሉን ሀሳብን ለማንበብ ቀጥሎ ያለውን ሰንሰለት ይጫኑ።* ልማታዊ ፓትርያርክ ]

ህዝብ ተረጋግቶ ተዋዶ ተስማምቶ የሰየመው፤ ለህዝብ የሚያስብ መንግስት ያቀደው፤ ጠበብቶች የመሰከሩለትና በዜጎች ሙሉ ድጋፍ ላይ የተመሰረተ እውነተኛ ልማታዊ እቅድ ቢሆንም እንኳ፤ ህዝባቸውን የጎዱ እምነቱን የናዱ አቡነ ማትያስ፤ ለቤተ ክርስቲያናቸው ለህዝባቸው ክብር ተላልፈው ህይወታቸውን ከሚሰጡት ግብጻውያን ጋራ አንድ ነን ማለታቸው "ጅብ በማይታወቅበት አገር ሄዶ ቁርበት አንጥፉልኝ" ከሚለው ከጅቡ አዘናጊያ ዘዴ የተለየ አይደለም።

በዝክረ ሊቃውንት መጽሐፍ በሰፈሩት ቅኔዎቻቸው ሊቃውንት አበው እንዳስተማሩን። ጵጵስና ወደ ኢትዮጵያ በገባበት ዘመን፤ ለነ አቡነ ባስልዮስ የደስታ መግለጫ ሆኖ እንደ ጎረፈላቸው፤ ለነገረ መለኮት ማፍረሻ፤ ለቀኖና መደምሰሻ፤ ለህዝብ ማስለቀሻ፤ አገርን እንደ ጸሪቅ መቆራረሻ ከማድረግ እስኪገቱ ድረስ፤ ወይም አምላካችን እስኪያነሳቸው ድረስ፤ የነ አባ ማትያስን የ'ቁርበት አንጥፉልኝ' ፖለቲካ የሚያፈርስ የቅኔ ማእበል አላማጉረፍ፤ ያባቶቻችንን ውርስ መርሳት ነውና የሚያስነቅፍ ነው።

በሁለተኛው ክፍል እንገናኝ፦ **ይቆየን**

ሌሎችን ጦማሮች መቃኘት ከፈለጉ፤ የሚከተለዉን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ። :

http://www.medhanialemeotcks.org/